ሚስት - እርግጠኛ ለመሆን! ምን ያህል እኔን እንደምትወደኝና ለራስህ ጤና እንደምትጠነቀቅ... እናም ለርካሽ ተግባር እንደማትሯሯጥ ለማወቅ... ለመሆኑ በጣም ተበሳጨህ?

ባል - በጣምም አልተበሣጨሁም

ሚስት - በል እስቲ እዚህ ና

ባል - እም!

*******

## ገቢር አስራ ሁለት

ለእይታ

ሙክታር - (በጣም ይስቃል)

ኩምባ - (በጣም ይስቃል)

ሙክታር - ስምሽ ኩምባ ነው አይደል? ልክ ነኝ? በጣም ጥሩ

- ኩምባ - እኔና አንቺ ወደያዝኩት ሆቴል ክፍል አብረን ብንገዝ ምን ይመስልሻል?
- አ ቲሞቲ! ምን ዓይነት ጨዋታ ነው?

ቲሞቲ - ቂል ነህ! ሙክታር! ሰካራም ነህ

- ሚስትህ? - አይቻስ?

ሙክታር - ታዲያ ምንድነው እሱ?

- ሚስት ማለት ምንድነው? ኡኡቴ!

ሙክታርና ኩምባ - (ይስቃሉ)

ሙክታር - እንሂዳ! እሺ!

ኩምባ - አ አ አ!

- እስቲ አያለሁ! የታለ ታዲያ?

ቲሞቲ - ሙክታር ይህ ለአይቻ ነው።

- ጠንቀቅ! ሰማህ!

ሙክታር - ኡኡቴ!

ቲሞቲ - ሂ! ሙክታር! ምን ይሰማሃል?

ሙክታር - እስቲ ብቻዬን ልሁን!

- ማታ ምንድን ነበር ያደረግነው?

ቲሞቲ - እብድ ነህ!

ሙክታር - ምን ማለትህ ነው? - ምንድነው እሱ?

ቲሞቲ - ሙክታር! ስለጠጣህ ምን እንደሠራህ ረስተናል?

- ባለፈው ምሽት ሴተኛ አዳሪ ይዘህ ወደ ቤርን ገብተሃል
- ራስህን እንድትከላከል ይህን ኪስህ ውስጥ ከትቼ ነበር ለአይቻም ጭምር!

ሙክታር - አምላኬ! እኔ አላምንም!

- አገኘሁት! ተይዣለሁ:: ይህም የእኔ ጥፋት ነው

ቲሞቲ - አዳምጥ! እርሷ ወይም አንተ መያዛችሁ እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: በሦስት ወር ጊዜ በሚካሄደው በኤች.አይ.ቪ. ደም ምርመራ ብቻ ነው የሚታወቀው ተመርምረህ ተገኝቶብሃል ከተባለም እኔ ካንተ አልለይም ጓደኛዬ:: አሁን ግን እርግጠኛ እስክትሆን ድረስ ወደ አይቻ እንዳይዛመት ተከላከል፡፡

ሙክታር - ወደ እሷ የማስተላልፍበት ምንም ጉዳይ የለኝም፡፡ ግን እንዴት እነግራታለሁ::

*******

## ገቢር አስራ ሶስት

<u>ተዋጊው</u>

እናት - ልጄ! የት እየሄድክ ነው?

ተዋጊው - ኤድስን ልዋጋ መሄዴ ነው እናቴ፡፡ ያለምንም ፋታ ወንድሞቼን እና እህቶቼን እያጠፋ ነው ስለዚህ ጦርነት ላውጅበት ነው የምሄደው

ተዋጊው - ና ውጣ! ኤድስ ወዲህ ና የት ነው ያለኸው?

ፖሊስ (ወንድ) - እዚያ ቁም!

ተዋጊው - ሄይ ኤድስ ኤድስን እየፈለግሁት ነው የት ነው የተደበቀው?

ፖሊስ (ወንድ) - እብድ ነህ? ሂድ! ሂድ ከዚህ! ሞኝ

ተዋጊው - መግደል እንድችል ኤድስን እየፈለግሁት ነው

- ሄይ! ወይዘሪት

ልጃገረድ - እሺ! ምን ትፈልጋለህ?

ተዋጊው - ቆንጆ ነሽ! በጣም ቆንጆ!

ልጃገረድ - ገንዘብ አለህ?

ተዋጊው - ገንዘብ ነው! ያው እዩ

ልጃገረድ - ይህ ብቻ ነው! በጣም ብዙ አይደለም::

- እሺ! የፍቅር ጓንት አለህ?